# መኖር ሞት ከሆነ (ድህረ-ምርጫ ግጥም)

ከአስታጥቄ ነፃነት ዘታች ጋይንት

ምነዋ ፈጣሪ!? ዕድሜዬ ረዘመ?!
በሶስት ሥርዓቶች፣ ቀሰለ ደከመ፣
በጃንሆይ ጊዜ፣ ምስለኔው አዘዘኝ፣
በደርግ ግዛትም፣ ቀበሌው ደገመኝ፣
በወያኔ ደግሞ፣ ህዳሴው ተጫነኝ፣
በሶስቱም ሥርዓቶች፣ ምረጡ ይሉናል፣
በዴሞክራሲ ስም፣ ይወተውቱናል፣
የምርጫ ምልክት፣ ተመርጦ ሲነገር፣
በጃንሆይ ጊዜ፣ እንደልብ ነበር፣
በደርግ ውድድር፣ ተመራጩ አንድ ነው፣
ማቸነፍ የሚችል፣ ዝሆኑ ብቻ ነው፣
በወያኔም ጊዜ፣ ድንጉል ወይም ንብ ነው፣
የደርጉ ድርጅት፣ በግልጽ ሲሰራ፣
በጣም ውስብስብ ነው፣ የወያኔው ሴራ፣
ውሻው በቀደደው፣ የቀበሌ አሰራር፣
ጅብ ገባበትና፣ ዘልቆ ዳር እስከዳር፣
ከተራው ቦዘኔ፣ እስከ ጦር ወታደር፣
አንዱን በሌላው ላይ፣ ተመልካች በመፍጠር፣
ለክፉ ባርነት፣ ተዳረገች ሀገር።

ታዲያ የኔ ቢጤው፣ በውስጥ በውጭ ያለው፣
ስንዴውን ከእንክዳድ፣ መለየት ያቃተው፣
ስሌቱ ጠፍቶበት፣ ግራ የተጋባው፣
ወይ አይተማመን፣ አንድነት አይገዛው፣
በየምርጫ ቦታው፣ ተባዝቶ ሲሰለፍ፣
በንብ፣ በድንጉሉ፣ እንደዚህ ቢነደፍ፣
"ይገፈፋል እንጂ፣ ምነው አይገፈፍ፣
"የማያውቅበትን፣ ይዞ ሲንከረፈፍ?!፣"
የሚለው ምሳሌ፣ ከቶ የት ላይ ይረፍ!

ለጉድ የጎለተኝ፣ የዕድሜው ባለፀጋ፣
ስንቱን ልታዘበው፣ ሲመሽም ሲነጋ፣
ከሁሉም ከሁሉም፣ የዘንድሮው ባሰ፣
ያምባ ገነን ዘመን፣ ህዳሴ ነገሰ፣
ይህ መከረኛ ሕዝብ፣ ሌላ ባህል ተውሶ፣
በውድም በግድም፣ ድምጹን ቢቀማ አንሶ፣
እንዴት ዝፈን ይባል?! በሰልፍ ተቀስቅሶ?!
እንደሚሉት ሁሉ፣ "እግዜር ዘፈን ሲያምረው፣"
አጠገበውና፣ ይኸው አስጨፈረው፣
እኔን ያስገረመኝ፣ የነመለስ ሴራ፣
ሀኅስ በጠገበ፣ የለታ ጭፍራ?!

ገብራይ በገደለ፣ የከማል ፉከራ?!
እኔን የገረመኝ፣ የክፉ ስርዓቱ!
ተክላይ በጠገበ፣ ገረመው ማግሳቱ?!

አዬ ዴሞክራሲ! አዬ ተሃዲሶ!
ትርጉም እንደሌለው፣ እንደ ሞኝ ልቅሶ፣
“ድምፃችን ይከበር፣” መልሶ መላልሶ፣
“እየዬም አትበሉ፣ እንደው ቅበሩኝ”
“ሳውቀው ገብቻለሁ፣ ዘመድ ሲመክረኝ፣”
እንዳለችዋ ሴት፣ በጣም ተፀጽታ፣
ምንም አይጠቅመንም፣ ያሁኑ ቱማታ!
ክልል ሰለሞኖች፣ ባገር ስለበዙ፣
የወያኔ መተት፣ አፍዝ አደንግዙ፣
ገና፣ ገና፣ ገና … ብዙ ነው መዘዙ፣
ሕዝብ እየተራበ፣ ጠገብክ ከተባለ፣
ከዚህ የሚከፋ፣ በሽታ የት አለ?!

የምርጫውን ነገር፣ ደጋግመን አይተናል፣
በሌላው አማራጭ፣ ብናብር ይሻላል፣
ይህ የሽንፈት ሰላም፣ ከንቆቆ ‘ሚመረው፣
ህዝብና ሀገርን፣ በልቶ ሳይጨርሰው፣
ከተጣባው ኮሶ፣ የሚገላግለው፣
የትግል መንገዱ፣ ከ’ንግዲህ አንድ ነው፣
መኖር ሞት ከሆነ፣ መሞትም ሕይወት ነው!

ግንቦት 2002 ዓ. ም.